## መስጠት የነፃነት ምንጭ ናት!!

አማኞች በእግዚአብሔር ጸጋ ጸድቀናል **(ሮሜ 3፡24)**፤ ሰላም አጊንተናል **(ሮሜ 5፡1)**፤ ድነናል **(ኤፌ 2፡8)**፤ ሕይወት ተቀብለናል **(ኤፌ 2፡4-5)**። ክርስቶስ በሞቱ ከኃጢአትና ከሕግ ነፃ አውጥቶናል **(ሮሜ 6፡4-6፣ 7፡6)**። እኛ ነፃ እንድንሆን ጌታ ዋጋ መክፈሉን መርሳት የለብንም።

ሆቴል ገብተህ ምትፈልገውን ተጠቅመህ ስትጨርስ "ሂሳብ ተከፍሏል" ከተባልክ አንተ ነፃ ነህ። ነፃ እንድትወጣ ግን ገንዘቡን የሰጠልህ ሰው እንዳለ አትርሳ። ያገኘኸው ነፃነት ምንጩ መስጠት እንደ ሆነ አትዘንጋ። ኢየሱስም ራሱን ሰጥቶ ነው ከኃጢአት እስራትና ከሕግ ባርነት ነፃ ያወጣን። የሚከተሉት ጥቅሶች ስለዚህ ሀሳብ የሚሉት አላቸው፡-

"ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መስዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።" **(ኤፌ 5፡2)**

"በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን …" **(ገላ 5፡1)**

ክርስቶስ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ፤ እኛም ነፃ ወጣን። ገልብጠን ብናስበው፣ ጌታ ራሱን ባይሰጥ እኛ እስካሁን ባሪያዎች ነበርን። መስጠት በሌለበት ነፃነት የለምና። ነፃነት የመስጠት ውጤት ናት፤ መስጠት የነፃነት ምንጭ ናት።

ጳውሎስ ክርስቶስ ነፃ ያወጣን እኛ በነፃነት እንድንኖር መሆኑን ነግሮናል። ይህ ማለት ነፃነት ዕለት ዕለት የሚኖር የሕይወት ዘይቤ ነው እንጂ በዘመቻ የሚደረግ አዋጅ ወይም በአመት አንዴ ታስቦ የሚውል ቀን አይደለም። እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያለው ዓላማ በሰጠን ነፃነት እንድንኖርለት ነው። ሆኖም ብዙዎቻችን ነፃ እንደወጣን ከማወጅ በዘለለ ነፃ ሕይወትን ለመኖር ስንቸገር ይስተዋላል።

ነፃ የወጣነው በመስጠት ከሆነ እንግዲያውስ በነፃነት ለመኖር እየሰጠን መኖር የግድ ነው። መጽሐፉ ክርስቶስ ስለ እኛ ራሱን ለሞት አሳልፎ መስጠቱን ሲነግረን እኛም ራሳችንን በመስጠት ልንመስለው እንደሚገባ አብሮ እንደ ነገረን አንርሳ። ክርስቶስ ራሱን ሰጥቶ ነፃነት የሚባልን ውጤት ካመጣ በነፃነት ሊኖር የሚወድ ራሱን በመስጠት ክርስቶስን ሊመስለው ይገባል። የእግዚአብሔር ቃል ራሳችንን እንድንሰጥ የሚያበረታታን በዚህ ምክንያት ነው።

"እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፡- ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ፣ እርሱም ለአዕምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።" **(ሮሜ 12፡1)**

እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት ዋጋ ሲከፍልልን ዓላማው የእኛ በነፃነት መኖር ነው። በነፃነት መኖር የሚቻለው ደግሞ ራስን በመስጠት ነውና እግዚአብሔር ከሁሉ በፊት ራሳችንን እንሰጠው ዘንድ ይወዳል። ራሱን የሰጠ አብሮ ጊዜውን፣ ጉልበቱን እና ገንዘቡን መስጠቱ አይቀርም፤ እነዚህ ሁሉ የእሱ ናቸውና።

ሆኖም እነዚህን አለመስጠት ራስን መከልከል ነው። ነፃነትን ሊኖራት የሚሻ ግን ራሱን በመስጠት ይጀምራል፤ ጊዜውን፣ ጉልበቱንና ገንዘቡን መስጠትም ይከተሉታል።

የመቄዶንያ አማኞች ይህ የገባቸው ይመስላል። እነዚህ ሰዎች በብዙ መከራና በጥልቅ ድህነት ውስጥ ነበሩ። ሆኖም የገቡበት መከራ ያላቸውን ከመስጠት አልከለከላቸውም። የነበሩበት ድህነት ለጋስ ከመሆን አላገዳቸውም **(2ቆሮ 8፡1-4)**። እንዲህ ያለን ሕይወት እንዴት መኖር ቻሉ?? ከተባለም መልሱ የሚከተለው ነው፡-

"አስቀድመውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታ ለእኛም ሰጡ እንጂ እንዳሰብነ አይደለም።" **(2ቆሮ 8፡5)**

ራስን በመስጠት ኢየሱስን የመሰሉ አማኞች ከፈለግን የመቄዶንያ ሰዎች ዓይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ያሉበት ድህነት ገንዘባቸውን ከመስጠት ያላገዳቸው ራሳቸውን በመስጠት ስለ ጀመሩ ነው። እግዚአብሔርን ለማገልገል ለጊዜአችን ከሳሳን፣ ለገንዘባችን ከተንሰፈሰፍን መሠረታዊ ችግራችን ራሳችንን አለመስጠታችን ነው። ይህ የነፃነትን ሕይወት እንዳንኖር እንቅፋት ነውና እንደ መቄዶንያ ሰዎች ራሳችንን በመስጠት እንጀምር፤ ሌላውም ተከትሎት መምጣቱ አይቀርም።

እግዚአብሔርን ለማገልገል የቆረጠ ጊዜውን፣ ጉልበቱን እና ገንዘቡን ይሰጣል፤ ራሱን ከሰጠና ነፃነቱን ለማጣጣም ከወሰነ አማኝ የሚጠበቀው ይህ ነውና። ራስን ከልክሎ፣ ጊዜን እምቢ ብሎ፣ ገንዘብ አልሰጥ ብሎ ግን ነፃነትን ለመኖር መመኘት መጥገብ እየፈለጉ አለመብላት ነው፤ መርካት እየወደዱ አለመጠጣት ነው። መስጠትን መለማመድ እንጀምርና ነፃነትን እንኑራት። አንርሳ! ነፃነት የመስጠት ውጤት ናት፤ መስጠት የነፃነት ምንጭ ናት!

**ቢኒያም በርሄ**

**የ "ከበፊት እስከ ወደፊት" መጽሐፍ ጸሀፊ**

**ነሀሴ 5/ 2014**